# የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች እና ኢሕአዴግ፤ ከዚኽ ወዴት?

*ከአያል ሰው ደሴ፦ የግል አስተያየት*

***<u>ክፍል አሥራ-አራት</u>*** *<u>(ከክፍል አሥራ-ሦስት የቀጠለ)፦...</u>*

በዚኽም መሠረት ምንም እንኳን ድርጅቶች በተናጠል የሚያደርጉት ትግል በተባበረና በተቀናጀ መልክ መሆን ይችል ዘንድ የጋራ ብሔራዊ ግንባር (ትብብር) እንዲመሠርቱ በብዙ ቅን-አሣቢ፣ ዴሞክራትና አገር-ወዳድ ወገኖች በኩል ሙከራዎች ያልተቋረጡ ቢሆንም በተለይ ኢአጉ ከተመሠረተበት ከሰማንያ-ዘጠኝ ዓ/ም ጀምሮ ድርጅቶች የትግል ግንባር እንዲፈጥሩ የእንቅስቃሴው ዋና ነጥብ (አጀንዳ) አድርጎ መያዙና ያላሰለሰ ጥረት ማድረጉ ይታወቃል። ድርጅቶችም በተለያየ መልክና ደረጃ ይኽንኑ የመሰባሰብ ጥረት የእንቅስቃሴአቸው አካል አድርገው ማየትን አላቆሙም። (ድርጅቶችን እናቀራርባለን ብለው ከሞከሩ አንዳንድ ወገኖች መኻል አንድ ቡድን ተነሣሁበት ያለውን ዓላማ ገልብጦ እራሡን ድርጅት ያደረገ እንደ-ነበርም ይታወሳል።) የሆነ ሆኖ ድኅረ-ኢተፖድጎ በተናጠልና የኅንዮሽ፣ አልፎ-አልፎም በርከት ብሎ በመገናኘት ሲደረግ የቆየው ኃይሎችን የማሰባሰብ ጥረት ድርጅቶች "የስደት-ሽግግር-መንግሥት" ማቋቋምን ግቡ ያደረገ 'ብሔራዊ የጋራ ግንባር' እንዲመሠርቱ ከልብ ታስቦ በኢአጉ የተጠራውና በፔንታጎን ሲቲ ደብል ትሪ ሆቴል የተካሄደው ስብሰባ ጉዳዩን በአዲስ መልክና መንፈስ እንዲታይ መነሾ ሆኗል ማለት ይቻላል።

እያንዳንዱ የጋራ ትግል መድረክ የየራሱ የሆኑ ባኅሪያት እንዳሉትና እንደሚኖሩት የታወቀ ቢሆንም፤ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) ከኢዴኃቅ ጀምሮ ምናልባትም እስካሁን ድረስ ከተደረጉ የጋራ ትግል መድረኮች ሁሉ በአመሠራረትና በአደረጃጀት፣ በአወቃቀርና በትግል-ምሪት፣ እቅድ፣ ስልትና አካሄድ (ስልትና ስትራተጂ) ለየት ያለ ነው ማለት ይቻላል። በአንዳንድ ተጠያቂነትም እንኳን ባይሆን ኃላፊነት ይሰማቸዋል ከሚባሉ ወገኖች ሣይቀር ስለ ኢዴኃኅ ብዙ ብዙ የተዛቡ አባባሎችና መሥመር የሣቱ ትችቶች በጽሑፍ ሣይቀር መቅረባቸው ይታወቃል። ከነዚኽ ውስጥ "ግንቦት 7" በሚል ርዕስ በአቶ ክፍሉ ታደሰ የተደረሰ በአብዛኛው መወድሰ-ቀስተ-ደመና ሊባል የሚችል "መጽሐፍ" አንዱ ነው። አቶ ክፍሉ ጨርሶ ባልገባቸውና በማያገባቸው የድርጅቱ ጉዳይ ገብተው በዚኽ ሁለት መቶ አምሣ ገጾችን የያዘ ኅቶት ውስጥ ቢያንድ በሰላሣ-አንድ ገጾች ላይ በተለያዩ መልኮች ኅብረቱን ያንኳሰሱና ስለ ኅብረቱ የተዛቡ፣ ያጠየሙና ከዚያም ያለፉ አስተያየቶችንና አባባሎችን ሰንዝረዋል፤ አንዳንድ ሃቆችንም በግርንቢጥ አቅርበዋል። አቶ ክፍሉ እነዚያን "እውነታዎች" ለማጣራት ሣይችሉ ቀርተው ግን እንዳልሆነ የዚያኑ ያኽል ግልጥ ነው። ከሌሎች ወገኖችም እንዲሁ የተዛቡ አስተያየቶች ተደምጠዋል፣ በጽሑፍ ላይም ሰፍረዋል። ለምሣሌ በአንድ ወቅት በውጭ-አገር የቅንጅት ተካዮች ከነበሩት መኻል አንዱ አቶ ብርሃነ መዋ 'መብት' በተሰኘ የራዲዮ ስርጭት ላይ ባስተላለፉት ትችት "ኅብረቱ ለቅንጅት መሪዎች እስር ቤት መግባት ተጠያቂ ነው" የሚል የክስ ጣት ቀሣሪና ምንም ዓይነት እውነታነት የሌለውና አስጠያቂ፣ አልፎም አሣዛኝ አባባል በአብነት ተጠቃሽ ነው። በአንዳንዶችም የኅብረቱን አቋም በትክክል ካለመረዳት የተነሣ ኢዴኃኅ "በአገሪቱ ላለው የኢሕአዴግ የጎሣ ፌደሬሽን የቆመ፣ ... የኢአዴግ ሕገ-መንግሥት እንዲቀየር የማይፈልግ፣ ወዘተ..." የሚሉ ከሃቅ የራቁ አንደምታዊ አስተያየቶች ሲሰነዘሩ ተስተውለዋል። አብዛኛው አሉታዊ አባባል አንድም የኅብረቱን መሠረታዊ አቋሞች ካለማወቅ፣ የፖለቲካና የኤኮኖሚ አማራጭ ሰነዶቹን ጨርሶ ዞር-ብሎ ካለማየት፣ ሌላም እያንዳንዱ ካለው በሌጣው የቆመ አስተሣሰብና ግልብ አንደምታዊ ስሜት የመነጨ እንደሆነ ግልጥ ነው። በእርግጥ በኅብረቱ ከታቀፉት ድርጅቶች ውስጥ በመጨረሻው አባባል (በአገዛዙ የጎሣ ፌደሬሽንና ለዚኹ ባለቤት ከሆነው "ሕገ-መንግሥት") የሚስማሙ የሉም ማለት አይደለም። ሆኖም የምንናገረው ስለ ኅብረቱ (ኢዴኃኅ) ሲሆን ግን ኅብረቱ መታየትና መገምገም ያለበት

በኅብረት ደረጃ ካለው አቋም አኳያ ሊሆን ይገባል፡፡ ለማንኛውም የዚኽ ጽሑፍ ዓላማ ሕዝባዊ ትግሉ የኃይሎች መሰባሰብን የግድ ስለሚል፤ ቀጣይ የጋራ ጥረቶች ካለፉት አንዳንድ ልምዶችን ሊያገኙ ይችላሉ ከሚል አስተሣሰብ ብቻ በመነሣት የተደረጉ ሙከራዎችን ለማሣየት የቀረበ እንጂ ቢያንስ አንድ የዳጎሠ መፀሐፍ ሊወጣው ስለሚችል የኢዴኃን ታሪክ እዚኽ ላይ በዝርዝር ለማስቀመጥ ባለመሆኑ፣ ስለ አመሠራረቱ፣ ይዘቱና ሂደቱ በአጭር በአጭሩ እነሆ፡፡

አንደኛ አመሠራረትና አደረጃጀት፤ ሀ) ዝግጅት፡- ከላይ እንደተጠቀሰው በወቅቱ በኢአጉ የተጠራው ስብሰባ ላይ የቀረበውን "የስደት-የሽግግር-መንግሥት" መመሥረት ወደሚያስችል ጠንካራ የተቃዋሚው አንድነት መሄድና ወዲያውኑ እውን ማድረግ የሚለው አቀራረብ በመርኀና በአካሄድ ደረጃ እንደማይቻል ለብዙዎቻችን ግልጥ የመሆኑን ያኽል፤ በሌላ በኩል ግን በተቃዋሚው ጎራ የተሠለፉ ኃይሎች ጠንካራ ኅብረት የመፍጠራቸው ጉዳይ እንዲሁ የሚተው አልነበረም፤ ቀደም-ሲል እንደተጠቀሰውም በዚያ አኳያ ጥረቶች አቁመው አያውቁም፡፡ በአገራችን ላይ ለውጥ እንዲኖር ከተፈለገና በወቅቱም ያንዣበበው ማዕከላዊ የአመራር እጦት ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ አሳሳቢነት በመገንዘብ ብሔራዊ አቅጣጫ (አጀንዳ) ሊነድፍና ሊቀይስ የሚችል የድርጅቶች መሰባሰብ እንዲፈጠር ማድረጉ የምር ትኩረትን የሚሻና ምርጫም የሌለው ጉዳይ ነበር፡፡ ኢዴኃቅ ውስጥ ለነበርን ኃይሎች ግን ያ መሰባሰብ የአስተሣሰብ ለውጥ ላይ ሊመሠረት፣ ሰከን ብሎ ሊመረመርና ረጋ ብሎ ሊጤን እንደሚኖርበትና እንደሚገባ ገና ከጠዋቱ ግልጥ ነበር፡፡ ስለሆነም ጉዳዩን ከሥር-መሠረቱ ለመርመርና በአዲስ ቅኝት ለማየት በመኻላችን መግባባቱ ነበር፡፡

ስለሆነም፣ ቀደም-ሲል ከኢዴኃቅ እስከ ኢተፖድኅ ድረስ ከተደረጉ የጋራ ጥረቶች የተገኘውን ልምድ በመመርመር ሁሉንም ለለውጥ የቆሙ ኃይሎች ያቀፈ መሠረተ-ሠፊ ስብስብ መፈጠር ስለሚቻልበት የሰከነ ምክክር የሚደረግበትን ሁኔታ ለማመቻቸት በኢአጉ ስብሰባ ተካፋይ ከነበሩት መኻል ከኢሕአፓ፣ ከመኢሶን፣ ከኅብረ-ሕዝብ፣ ከደቡብ ኅብረት፣ ከአማራጭ-ኃይሎች እና ከትዴት የተውጣጣና በቅደም-ተከተል አቶ ፋሲካ በለጠን፣ አቶ ሙሉጌታ ኃይሉን፣ መ/አ አያል-ሰው ደሴን፣ አቶ ከድር መሐመድን፣ አቶ አሰፋ ደጳሶንና አቶ ተሾመ ጉዶ ፀጋዬን ያቀፈ አንድ ጊዚያዊ የክትትል (ፈታሽ) አካል (ኮሚቴ) ተቋቋመ፡፡ (በዚኽ ጊዚያዊ አካል ውስጥ አቶ አባ ብያ ከኦሮሞ ነፃ-አውጭ ድርጅት አልፎ-አልፎ ተሣታፊ ነበሩ፡፡) የጊዜኣዊ ፈታሽ ኮሚቴው ዓላማም በቅድሚያ አዲስ የኃይሎች መሰባሰብ አስፈላጊነትን ሁሉም እንዲያምንበትና ሙሉ ትኩረት ሰጥቶ በቅርበት በመመርመር ይኽንኑ ጉዳይ የሚከታተል ሁሉን-አቀፍ የጋራ አካል የሚቋቋምበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነበር፡፡ ለዚኽ ተልዕኮ እውን መሆን ጊዚያዊ አንቀሣቃሽ ኮሚቴው የመረጠው አካሄድ ምንም ዓይነት እርምጃ ከመወሰዱና አንዳች ውሳኔ ከመደረጉ በፊት ሁሉም ድርጅት ከጅምሩ የምክክሩ ተሣታፊ እንዲሆን የተቻለውን ጥረት ማድረግን ነበር፡፡ በዚኽ ጥረት አካሉ እስከ ሰኔ ስድስት ቀን ዘጠና-ሦስት ዓ/ም ድረስ ከተጓዘ በኋላ ለአሠራሩ የተሻለ ቅርፅ ለመስጠትና እንቅስቃሴውን ተጠያቂነት ባለው መልክ የምር ለመያያዝ እንዲችል በዚኹ ቀን ባደረገው ስብሰባ ዶ/ር ደስታ ዳምጠውን (ከኅብረ-ሕዝብ) ሊቀ-መንበር፣ አቶ ፋሲካ በለጠን (ከኢሕአፓ) ፀሐፊ እና አቶ ከድር መሐመድን (ከደቡብ ኅብረት) ምክትል ፀሐፊ በማድረግ ጊዚያዊ አመራር ሰይሞ ቢያንስ በሣምንት አንድ ጊዜ እየተገናኘ ዓላማውን እግቡ ለማድረስ የሚያስችሉ ምክክሮችን ማድረግና እቅዶችን ማውጣት ቀጠለ፡፡ በውሳኔውም መሠረት አሉ የሚባሉ የፖለቲካ ድርጅቶችን ሁሉ በመቅረብ ከተወካዮቻቸው ጋር በአካል በመገናኘትና የፊት ለፊት ውይይት በማድረግ ዓላማውን በማስረዳት የታሰበውን የተቃዋሚ ክፍል አጠቃላይ ስብሰባ ማዘጋጀት የሚችል ቋሚ የጋራ አካል እንዲቋቋምና በዝግጅቱም ከጅምሩ ሁሉም ተሣታፊ እንዲሆኑ ተስፋ ሣይቆርጥ ጠንክሮ ተንቀሣቅሷል፡፡

ይሁንናም ከጅምሩ ከነበሩት ስድስት ድርጅቶች በተጨማሪ (ኦነግ አልፎ-አልፎ በስብሰባዎች በሰባተኛነት መገኘቱ እንዳለ ሆኖ) የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ኅብረት (ኢዴኅ) በሻለቃ ኢያሱ አያልቅበት ተወክሎ ብዙ ሣይቆይ የእንቅስቃሴው አካል ሲሆን፤ ከነዚኽ ውጭ ለምክክር ከተቀረቡ ድርጅቶች ውስጥ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) ከአንዳንድ አባላቱ የሚደረገውን አሉታዊ ጫና ሁሉ ተቋቁሞ በጥቅምት ወር ዘጠና አምስት

ዓ/ም የተጀመረው የጋራ ጥረት አባል እስከ-ሆነበት ጊዜ ድረስ ሌላ በጎ ምላሽ የሰጠ ድርጅት አልነበረም። አንዳንድ ድርጅቶች የመሰባሰቡ ጥረት ውጤት ያመጣል የሚል እምነት የለንም የሚል ምክንያት እየሰጡ ለመተባበር ፈቃደኛ አልነበሩም። አልፎም አሉታዊ ቅስቀሣና አፍራሽ ዘመቻ የሚያደርጉም አልጠፉ። ጊዚያዊ አካሉ ከዓመት በላይ ጥረት ካደረገ በኋላ ተልዕኮውን የተሻለ መልክ አስይዞ ለማስቀጠል ቁርጠኛ አሣብ በማድረግና እስከ-መጨረሻው ለመግፋት በመወሰን በአዲስ መልክ “የፖለቲካ ድርጅቶች አገር-አቀፍ ጉባዔ አዘጋጅ ኮሚቴ” (All Party Conference Organizing Committee) በሚል ተደራጅቶ፣ ውስጠ-ደንቡንና የሥራ መመሪያውን በማውጣት፣ ሕጋዊ ፈቃድ በማግኘትና የእንቅስቃሴ እቅዱን በመንደፍ፣ ፈቃደኛ ሆነው ለሚገቡ ድርጅቶች በሩን ክፍት አድርጎ በሥርዓትና በትጋት ኃላፊነቱን ለመወጣት ሥራውን ቀጠለ። ያ እየሆነ አሁንም ድርጅት ለተባለ ሁሉ ስለ እንቅስቃሴው በጽሑፍ በማሣወቅና በጉዳዩ ላይ በአካልም ባመቸ መንገድም ከሚመለከታቸው የአመራር ክፍሎች ጋር እየተወያየ ዝግጅቱ በጋራ እንዲሆን የሚያደርገውን ዘመቻ አላቋረጠም። መድኅን እንቅስቃሴው ከተጀመረ ከዓመት ተኩል በኋላ በታኅሣስ አሥራ-ሁለት ቀን ዘጠና-አምስት ዓ/ም አዘጋጅ አካሉን በመቀላቀሉ የአባል ድርጅቶች ቁጥር ወደ ስምንት ከፍ አለ።

ኮሚቴው ቢያንስ በሣምንት አንድ ጊዜ እየተሰበሰበ ውይይትና ክርክር ያደርጋል፣ አዳዲስ እቅዶችን በማውጣትም የተደረሰባቸውን ውሳኔዎች በተግባር ይተረጉማል። አባል ድርጅቶች እኩል ድምፅና ኃላፊነት ሲኖራቸው፣ እያንዳንዱ አባል ድርጅት በአንድ ከፍተኛ የአመራር አባል በኮሚቴው ውስጥ በመወከል ይሣተፋል። እያንዳንዱ ተወካይም ኮሚቴውን በተራና በተዘዋዋሪነት ለአንድ ወር በሊቀ-መንበርነት የመምራት ኃላፊነት ነበረበት። አዘጋጅ አካሉ በውስጡ የሥራ ክፍፍል በማድረግ፤ በተለይ በሰነድ ዝግጅት፣ በሕዝብ ግንኙነትና በአቅም ግንባታና እርዳታ አሰባሰብ ዙሪያ ንዑስ አካሎችን አቋቁሞ ተንቀሣቅሷል። በአዘጋጅ አካሉ አባላት ዘንድ ይኸ መሰባሰብ የታሰበውን ውጤት እንዲያስገኝ የተቻለውን ያኽል መሠረተ-ሠፊ እንዲሆንና አግላይነት የሌለው እንዲሆን፣ መርኁን የጠበቀና ዓላማውንም የተከተለ፣ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻው ድረስ ሕዝቡ የእንቅስቃሴው አካል የሆነበትና ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያውያን ፍላጎትና እቅድ እንዲካሄድ፣ ነፃ ሆኖ እንዲቀጥልና ምንም ዓይነት የውጭ ኃይሎች ጣልቃ-ገብነትም ይሁን ጫና እንዳይኖርበት ለማድረግ በውስጣቸው መግባባት ነበር። ለዚኸም የእያንዳንዱ ተወካይ የመጀመሪያ ትግል የታሰበው የኃይሎች መሰባሰብ ፍሬ እንዲሰጥ ድርጅቶቻቸውና አባሎቻቸው የእንቅስቃሴውን ዓላማ በተገቢ ተረድተው ሙሉ ድጋፋቸውን እንዳይነፍጉና ሙሉ ትኩረት ሰጥተው ኃይላቸውን፣ አቅማቸውንና ጉልበታቸውን በዚኹ የጋራ ጥረት ላይ እንዲያውሉ ማስቻል ነበር። በዚኽ ረገድ ሁሉም ድርጅቶች የሚችሉትን ሁሉ ማድረጋቸው ይታወቃል። (በተለይም ኢሕአፓ ጊዚያዊ ኮሚቴው ከተቋቋመበት ከሰኔ ስድስት ቀን ዘጠና-ሦስት ዓ/ም ጀምሮ እስከ ሁለት-ሺህ ዓ/ም ድረስ (ለሰባት ዓመታት) ጽ/ቤቱን (ቢሮውን) ከሙሉ መገልገያዎች ጋር በመጀመሪያ አዘጋጅ ኮሚቴው በመቀጠልም ኅብረቱ ያለ-አንዳች ወጭ ገላቸውን-ሰደውና እንደ ራሣቸው ንብረት ቆጥረው እንዲጠቀሙበት አስችሏል፣ አባላቱም በየ ድጋፍ ኮሚቴዎችና የኅብረቱ እንቅስቃሴዎች ሙሉ ተሣታፊ እንዲሆኑ አድርጓል።)

የአዘጋጅ ኮሚቴው አባላት የተለያዩ ድርጅቶች ተወካዮች እንደመሆናቸውና የተለያዩ ልምዶች ያሏቸው በመሆናቸው በመኻላቸው አንዳንድ አለመጣጣሞች መከሰታቸው የሚጠበቅ ቢሆንም፣ አብረው እየሠሩ በቀጠሉ ቁጥርና ዋናው ንጥጥራቸውም ከተናጠል የድርጅት አቋማቸው በላይ በሆነው የጋራ ዓላማ ላይ በመሆኑ፣ መቀራረብንና መተማመንን እያዳበሩ በመሄዳቸው፣ መከባበሩና አብዛኛውን ጊዜ የአሣብ አንድነት ማኅልበታቸው፣ አልፎ አልፎ የሚነሱ የአሣብ ልዩነቶችን ተደማምጦ ለመግባባትና ለጋራ ውሳኔ ተገዥ ለመሆን አልፎም እንደ አንድ ድርጅት አባል ተያይቶ ለመሥራት ችለዋል። ከሞላ-ጎደል ሁሉም የአዘጋጅ ኮሚቴው አባላት በእንቅስቃሴው ከነበራቸው የጠና እምነትና እንዲሣካም ከነበራቸው የጋለ ፍላጎት የተነሣ ምናልባት ድርጅቶቻቸው የጋራውን ጥረት ሙሉ-በሙሉ የማይደግፉ ወይም የሚያፈነግጡ ቢሆን ድርጅታቸውን ጥለው እስከ-መሄድ እንደሚችሉ ቁርጠኝነት ነበራቸው ማለት ይቻላል። ኮሚቴው በአዲስ መልክ ተደራጅቶና ሕጋዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ ፈቃድ እንዳገኘ ጊዜ ሣይፈጅ በዚኽ አገራዊ የጋራ ጥረት ላይ

ኢትዮጵያውያን በያሉበት ገና ከጅምሩ ቀጥተኛ ተሣታፊ እንዲሆኑ ወስኖ የድጋፍ አካሎችን (ኮሚቴዎችን) በብዙ አካባቢዎች ማቋቋም ችሏል፡፡

ኮሚቴው ሁሉንም በኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባኛል-ባይ ድርጅቶች የእንቅስቃሴው ተሣታፊ ለማድረግ አሣቡና ውሳኔው በመሆኑ፣ ከእምነት ቤቶች ጀምሮ በልዩ ልዩ የኅብረተሰባችን ክፍሎች ጥቅም ዙሪያ የተሰባሰቡ ወገኖችን ሙሉ ትብብርና እገዛ ለማስገኘት፣ ምሁራን ጉዳዩን አውቀው ድጋፋቸውና ተሣትፎኣቸው እንዳይለይ ለማስቻል ኮሚቴው ቀጠሮ እየያዘ እያንዳንዱን በፊት ለፊት በማግኘትና ስለ እንቅስቃሴው ዓላማ በማስረዳት ትብብራቸው እንዳይለየው ጠንክሮ ተንቀሣቅሷል፡፡ በዚኽም መሠረት ትልቅ ትንሽ ሣይባል ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያናት ጀምሮ የሁሉንም እምነት ተከታዮች፣ ምሑራንን፣ ታዋቂ ግለ-ሰቦችን፣ የፖለቲካ-ነዛሪዎችን (political activists)፣ ልዩ ልዩ ስብስቦችን፣ የኪነት ሰዎችን፣ በኢትዮጵያውያን የሚካሄዱና የሚመሩ በውጭ አገር የሚገኙ ልዩ ልዩ የራዲዮ ጣቢያዎች ኃላፊዎችን፣ የድረ-ገፆችና የጋዜጦች አዘጋጅዎችን፣ ወዘተ.. በደብዳቤ በማሣወቅና በአካል በመገናኘት በአገሪቱ ያለውን ሁኔታ ተረድተውና አዎንታዊ ለውጥ እንዲገኝ የኃይሎች መሰባሰብ አስፈላጊ መሆኑን ተገንዝበው እርዳታቸውንና ትብብራቸውን ለዚኹ ጥረት እንዲለግሱ ከፍተኛ ሙከራና እንቅስቃሴ ተደርጓል፡፡ በተናጠልና በቡድን በቡድን ስብሰባዎች እያደረገም ጥልቅ የአሣብ ልውውጥና ውይይት አድርጓል፡፡ እንደ ኢአጉ የመሣሰሉ ጉዳዩን የራሣቸው አድርገው የቆጠሩና ጥረቱን ከጅምሩ የደገፉ ወገኖችም ለእንቅስቃሴው መነሻ የሚሆን ገንዘብ ከመለገሥ ጀምሮ ሙሉ ትብብራቸውን ሰጥተዋል፡፡

እንቅስቃሴው ሠፊ-መሠረትና የሕዝብ ድጋፍ እንዲኖረው በተለይ ኢትዮጵያውያን በርከት ብለው በሚገኙባቸው ቦታዎች ሕዝባዊ ስብሰባዎችን በማድረግ ስለ አገራችን ሁኔታና ስለ-ኅብረት ትግል አስፈላጊነት ውይይቶች ተደርገዋል፡፡ ኮሚቴው በድጋፍ ኮሚቴዎች አማካይነትም ሆነ በግለሰብ ደረጃ ከወገን ኢትዮጵያውያን የገንዘብ እርዳታ ብቻ ሣይሆን አሣቦችንና አስተያየቶችን እንዲቀርቡ እየጠየቀ ለጋራ ሰነድ ዝግጅቱ፣ ለአሠራሩና ለአካሄዱ ብዙ ጠቃሚ አስተያየቶችና ምክሮች ተለግሰውታል፡፡ የባንክ ሂሣቡንም ከፍቶ እርዳታዎች መጠየቅና ከመቶ-ሃያ ሽህ የአሜሪካን ብር (ዶላር) በላይ ከወገን ኢትዮጵያውያን ማሰባሰብ በመቻሉ፣ ኮሚቴው ከጅምር እንዳቀደው ዝግጅቱም ሆነ ኅብረቱን የፈጠረው ጉባዔ ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያውያን አቅም እንዲሆን ለማድረግ ችሏል፡፡ በተመሣሣይ ሁኔታ እንቅስቃሴው አስተማማኝ ቀጣይነት እንደሚኖረውና ወደ-ኋላ የማይመለስበት ደረጃ ላይ መድረሱን ኮሚቴው ሲረዳ፤ በኢትዮጵያና በዴሞክራሲ ሥርዓት እውን መሆን ጉዳይ ላይ ቀጥተኛም ተዘዋዋሪም ትሥሥር የሚኖራቸውና ለተጀመረው በጎ ጥረትም አስተዋፅዖ ይኖራቸዋል ተብለው ለታሰቡ የውጭ መንግሥታትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ክፍሎች (በተለይ አሜሪካ፣ ካናዳና አውሮጳ) ስለ እንቅስቃሴው እንዲያውቁ ለማድረግ የተቀናበረ ዘመቻ ተደርጓል፡፡ የሚደረገውን ጥረት ከአሜሪካ መንግሥት ጀምሮ ብዙዎቹ ከዚያ በፊት ከተደረጉ ሙከራዎች የተለዩ ሊሆን አይችልም ከሚልና በተቃዋሚው ጎራ አንድ ሆኖ የመሥራት ፍላጎትና ብቃት ላይ ካላቸው ዝቅተኛ አመለካከት በመነሣት ይኽንንም ያዩት እስከ-መጨረሻው አይገፋበትም በሚል የጥርጣሬ ዓይን መሆኑ የተጠበቀ ነበር፡፡ እየቆየ ግን እንቅስቃሴው እንደተለመደው ድርጅቶቹ በተናጠል የሚያደርጉት ሣይሆን ኅብረተሰቡ ያቀፈውና ተሣታፊ እየሆነ ያለበት መሆኑን ሲረዱና ኮሚቴውም የሚያስተላልፋቸውን መልዕክቶች ይዘት በመገንዘብና ቁርጠኝነቱን በማየት የሚጠየቁትን ለማዳመጥ ብቻ ሣይሆን እርዳታና ትብብር ለማድረግም ፈቃደኛነታቸውን መግለጣቸው አልቀረም፡፡ በተለይ የጉባዔው ቀን እየተቃረበ ሲመጣ ብዙዎቹ ያሣዩት አክብሮትና በጎ-ፈቃድ ከፍተኛ ነበር፡፡

የምኁራንን ቀጥተኛ ትብብርና ተሣትፎ በመሻት በልዩ ልዩ ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ ጥናታዊ ጽሑፎች እንዲዘጋጁ በማድረግ፤ በመጨረሻም በአባል ድርጅቶች የቀረቡ ጥናቶችን በማካተት የመሰባሰቢያና የመሥሪያ የጋራ ሰነድ በማዘጋጀት ተካፋይ ለመሆን ዝግጁነትና በጎ-ፈቃድ ላሣዩ ድርጅቶች ሁሉ የሚጨመረውን ጨምረውና የሚቀነሰውን ቀንሰው እንዲያዳብሩት፣ እንዲያሻሽሉት ወይም ተለዋጭ ሰነድ እንዲያቀቡ ከማሣሰቢያ ጋር አስቀድሞ ሊላክላቸው ችሏል፡፡

***በክፍል አሥራ-አምስት ይቀጥላል......***